# ኢትዮጵያዊነት

# ለሁላችንም የሚሆን መመሪያ!

- በአንድ አገር ውስጥ የተወለደ ሁሉ መጠሪያው አንድ ነው፡፡
- አንድ ሰው አንድ መንደር ውስጥ ቢወለድም የመጨረሻ መጨረሻ ዜግነቱ በአገር ደረጃ ነው የሚገለጸው፡፡
- ስለሆነም አንድ ግለሰብም ሆነ ቡድን የብሄር መለያ አለኝ ቢልም የመጨረሻ መጨረሻ የአንድ አገር ዜጋ ነው፡፡
- ይህ ጉዳይ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነትን ያገኘና፣ ከአንድ አገር ክልል የተወለዱ ግለሰቦች መቀበል ያለባቸው ጉዳይ ነው፡፡

## የሚያገናኙን ነገሮች!

- የባህል ጉዳይ- እንደሚታወቀው ባህል በብዙ ነገሮች የሚገለጽ ነው፡፡
- ባህል አንድ ብሄረሰብ ወይም ጎሳ የሚያፈልቀውና የሚያዳብረው ሳይሆን የጥምር ውጤት ነው፡፡
- ስለሆነም አንድ ቦታ የፈለቀ ባህል ወደ ሌላ ቦታ በመተላለፍ ልዩ ዕምርታን ያገኛል፤ ይዳብራል፡፡
- የግዕዝ ፊደል መቀረጽና መዳበር፣ ከዚያም የአማርኛ ቋንቋ ሆኖ መጻፍና እስከዛሬ ድረስ መድረስ ልዩ ልዩ ብሄረሰቦች የተካፈሉበት ነው፡፡
- በተጨማሪም የምግብ አሰራር፣ ጠላና ጠጅ እንዲሁም ካቲካላ አጠማመቅ አንድ ቦታ ቢጀመሩም እየዳበሩ የመጡና ሁሉም የህብረተሰብ ክፍሎች የተቀበሏቸው ናቸው፡፡

- እንደዚሁም ሙዚቃና አለባበስ አንድ ቦታ በመዳበር፣ ጊዚያዊ በሆነ መልክ በመቃኘት የሁሉም የህብረተሰብ ክፍል መጠቀሚያ የሆነ ነው።
- ስለዚህም ይህኛው ባህል የአንድ ብሄረሰብ ብቻ ነው፣  የበላይነትን በመቀዳጀት ሌሎችን አፍኗል ማለት አይቻልም። ባህል ውስጣዊ ኃይል ያለውና እየተስፋፋ የሚመጣ ነው።
- ዕድገቱ  ወይንም መቀጨጩ ሊወሰን የሚችለው በአንድ አገር ውስጥ ባለ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ነው።

## የተሳሳተ ግንዛቤ  !

- የህብረ-ብሄር  ምስረታ ታሪካዊ ግዴታ ነው።
- ብዙ አገሮች ውጣ ውረድን አልፈው አንድ የጋራ አገር መስርተዋል።
- የህብረ-ብሄር ምስረታ በሰላም የተካሄደብት አገር የለም።
- በተለይም በአውሮፓ ምድር ውስጥ አገሮች ጥንካሬ ማግኘት የቻሉት አንደኛው ኃይል ሌላውን በማሸነፍ ብቻ ነው።
- የተለያዩ ብሄረ-ሰቦች ወይም ትናንሽ አገዛዞች ባይዋሃዱና በአንድ ባንዲራ ስር ባይጠቃለሉ ኖሮ የኢኮኖሚ ዕድገት፣ እንዲያም ሲል የሳይንስና የቴክኖሎጂ ምጥቀት ባልታየ ነበር።
- ስለዚህም ከመቶ ያሃ ዐመት በፊት የተለያዩ የአገራችን ክፍሎች ወይም ብሄረሶቦች በአንድ አገዛዝ ስር መጠቃለላቸው እንደ ወንጀል መቆጠር የለበትም።

- በአገራችን ምድር ውስጥ የህብረ-ብሄር ምስረታ ያልተጠናቀቀው በተለያዩ ምክንያቶች የተነሳ ነው።
- ሰፋ ባለ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ የተደገፈ አልነበረም።
- የማኑፋክቸር መሰረት አልነበረም። ሳይንስና ቴኮኖሎጂም ማዳበር አልተቻለም።
- ሰፋ ያለ ዘመናዊ ኢንስቲቱሽን በየቦታው ማቋቋም አልተቻለም።
- ሰፋ ያለ ምሁራዊ መሰረትና እንቅስቃሴ አልነበረም።
- የህብረ-ብሄር ምስረታ ጠለቅ ወዳለና ወደ ተሻለ ዘመናዊነት ከማምራት ይልቅ የፊዩዳል ስርዓት እንዲስፋፋ ያደረገ ነው።
- ከዚህ ጋር ተያይዞ ያልተስተካከለ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ በመስፋፋቱ ስርዓቱን ልዩ ገጽታ ሰጠው። በሌላ አነጋገር የተገለጸለት ህብረተሰብ ከመፈጠር ይልቅ የብሄረሰብ ጥያቄ እንደ ዋና አጀንዳ ሆኖ ቀረበ።
- በመሆኑም ኢትዮጵያ የብሄረሰቦች እስር ቤት ነች የሚለው ታሪክን ያላገናዘበ አነጋገር ስር እየሰደደ መጣ ።
- ይህ ጉዳይ ከብሄራዊ አጀንዳና በጋራ ጠላት ላይ፣ ማለትም ኋላ-ቀርነትና ድህነት ላይ ከመረባረብ ይልቅ አላስፈላጊ ፍጥጫ ውስጥ ከተተን።
- እንደሚታወቀው ድህነቱና ኋላቀርነቱ ከ90% በላይ የሚቆጠረውን ህዝባችንን የሚመለከት ነበር።
- እንደሚባለውና እንደሚናፈሰው አዲስ አበባ ላይ የተቀመጠው አገዛዝ አማራን የሚውክል ሳይሆን የፊዩዳሉን፣ የአሪስቶክራሲውንና የንጉሳውያኑን ቤተሰቦች ጥቅም የሚያስጠብቅ ነበር።

- እንደየደረጃቸውና እንደየአስተዋጽዖአቸው በገዢው መደብ ውስጥ ቢያንስ፣ የትግሬ፣ የኤርትራ የአማራና የኦሮሞ ብሄረሰቦች ተካፍለውበታል።
- እነዚህ ሁሉ በማወቅም ሆነ ባለማወቅ በአንድ በኩል ማዕከላዊ ግዛት እንዲጠነክር ያደረጉ ናቸው፡
- ለኢትዮጵያም መታወቂያ የሰጡ ናቸው።
- በሌላ ወገን ደግሞ የስርዓቱ ተጠቃሚዎች ናቸው።
- ስለሆነም በአፄ ምኒልክም ሆነ በአፄ ኃይለስላሴ ዘመን የሰፈነው አገዛዝ ከላይ የተጠቀሱትን ብሄረሰብ ተወካዮች የሚያጠቃልል ነበር።
- የአማራ የገዢ መደብ ነው ሲገዛን የነበረው የሚለው ቦታ የለውም። ሀቁን የሚያንጸባርቅ አይደለም።

## የችግሩን ምንጭ በሌላ መነጽር ያለማየት ጉዳይ !

- እንደዚህ ዐይነቱ አመለካከት የሚመነጨው የህብረተሰብ ሂደትንና አገነባብ ታሪክን በቅጡ ካለመረዳት የተነሳ ነው።
- አንድን ህብረተሰብ ከሌላው ጋር በማነፃፀር የተደረገ ግምገማና አቀራረብ አይደለም።
- በጠባብ አመለካከት ድምደማ የተደረሰበት ነው፡፤
- በተጨማሪም በሃያኛው ክፍለ-ዘመን አገራችን ብቻ ሳትሆን ብዙ የሶስተኛው ዓለም አገሮች የነበሩበትን ሁኔታና ከውጭ የሚመጣባቸውን ተጽዕኖና ግፊት ያላገናዘበ ነው።
- የካፒታሊዝም መስፋፋትና እንዲያም ሲል ወደ ኢምፔሪያሊዝምነት ተለውጦ እንደኛ ያሉ አገሮችን ማስጨነቁ አንደኛው የድህነት ምንጭ መሆኑ ለብዙዎቻችን ግልጽ አልነበረም።
- ስለሆነም ሁሉንም ነገር በጠባብ እንድንመለከትና ወደ ርስ በርስ ፍጥጫ ውስጥ መግባት ቻልን።

# አብዮቱ የፈጠረው ጥሩና አስቸጋሪ ሁኔታ!

- የአብዮት መፈንዳትና ጥገናዊ ለውጦች መካሄዳቸው ብዙ ነገሮችን ሊመልሱ ይችሉ ነበር።
- የአብዮቱና የጥገናው ለውጥ ትርጉምና ብሄራዊ ባህርይ ያልገባቸው ኃይሎች ጦርነት አወጁ።
- ቆም ብለው ከማጤንና ትንተና እየሰጡ በጋራ ወደሚያሰሩ ነገሮች ላይ ከማምራት ይልቅ ሁሉም በየፊናው መታገልን መረጠ።
- በመሰረቱ አብዮቱ ከፈነዳና ጥገናዊ ለውጦች ከታወጁ በኋላ በትግል ስም የተካሄደው ፍጥጫ ስልጣን ለመያዝ የተደረገ ትግል ነበር።
- ይህ ዐይነቱ የግንዛቤ ጉድለት ከውስጥ ሲቦረቡረን፣ ለውጭ ጠላት ደግሞ አጋልጦ ሰጠን።
- ኢትዮጵያን ለሚጠሉ የአካባቢው አገሮችና ኢምፔርያሊስት ኃይሎች አጋጣሚን አገኙ፡፡
- አገራችንን ከውስጥም ሆነ ከውጭ ማዳከም ጀመሩ።
- የቀይ ሽብርና የነጭ ሽብር ጉዳይ የነዚህ ሁሉ ውጤት ነው።
- የዚህ ሁሉ ዋናው ችግር የምሁሩ ጨቅላነት ነው።
- በሰፊው ለማሰብ የሚያስችለው ምርምር አለመኖሩ ነው።
- ስትራቴጂካዊ በሆነ መልክ ማሰብ አለመቻሉ ነው።
- በዚህም ዐይነቱ የጨቅላ አካሄድ በብዙ ሺህ የሚቆጠር ምሁርና በሚሊዮን የሚቆጠር ዜጋ አለቀ።
- ቤተሰብ፣ አገርና የታሪክ ቅርሰቶች ፈራረሱ።
- የዚህ ሁሉ ሌላው ችግር የብሄራዊ ከበርቴ መደብ አስተሳሰብ ያለው ኃይል አለመገኘቱ ነው።
- ይህ በሌለበት አገር ደግሞ ማንም እየተነሳ ይፈነጫል።
- በቡድን በቡድን በመደራጀት ፍጥጫ ውስጥ በመግባት አንድን አገር ወደ ጦር አውድማ ውስጥ ይከታታል።

## የወያኔ አገዛዝ የፈጠረው ችግር !!

- ወያኔ የታሪክ ግንዛቤ የሌለው፣ እንደሌሎች ሁሉ ድርጅቶች ከኢትዮጵያ ህዝብ አብራክ የፈለቀ ነው።
- ልዩ የሚያደርገው ከአንድ ብሄረሰብ የተውጣጣና ወደ ኋላ ከቀረ አካባቢ መምጣቱ አስተሳሰቡን ይወስናል።
- ከሌላው ጋር አለመጋባቱ፣ ከተለያዩ ብሄረሰቦች ጋር በመቀላቀል ልምዳቸውን አለመቅሰሙና አለመጋራቱ አስተሳሰቡን ውስን አድርገውታል።
- ስለሆነም በውስጥና በውጭ ኃይሎች ተደግፎ ስልጣን ከያዘ በኋላ የኢትዮጵያን ምንነት በመካድ አገሪቱን በፌዴራሊዝም ስም በክልል መከለልና ልዩ ዐይነት የብሄረሰብ ምልክት መስጠት ቻለ።
- በመሰረቱ ይህ አካሄድ ዲሞክራሲያዊና ዘመናዊ አይደለም።
- የሪፑብሊክን ምስረታ የሚያግዝና የሚያፋጥን አይደለም።
- ለከፈፍለህ ግዛ የሚያመችና ዋር ሎርዶች በየቦታው እየተፈጠሩ አስቸጋሪ ሁኔታ እንዲከሰት የሚያደርግ ነው።
- ኋላ-ቀርነትንና ድህነትን የሚያፋጣን ነው።
- በጆሮ ደግፍ ላይ ቆረቆር እንዲሉ በብዙ መልክ የሚገለጸውን ችግር ጥልቀት እንዲኖረው የሚያደርገው ነው።
- ብሄረሶቦች በየራሳቸው ቋንቋ እየተነጋገሩ እንዳይግባቡ የሚያደርግ ነው።
- አድማሳቸውን የሚያጠብና በዘለዓለም ብጥብጥ ውስጥ እንዲኖሩ የሚያደርግ ነው።
- ስለሆነም ለአገሪቱ ብቻ ሳይሆን ለአካባቢው አገሮች ጠንቅ የሆነ እጅግ አደገኛ የፖለቲካ ዘይቤ ነው።
- ስነ-ምግባርና ሞራል እንዳይዳብሩ የሚያደርግ ነው።
- የሀብት ዘረፋ እንዲካሄድ የሚያደርግ ነው።
- በመሆኑም ብሄረሶቦች በብሄረሰብ ደረጃ መካለላቸው አልጠቀማቸውም።
- የባስውኑ እንዲቀጭጩና ደሃ እንዲሆኑ፣ እንዲያም ሲል በራሳቸው ላይ እንዳይተማመኑ ነው የተደረጉት።

# የአቢይ አገዛዝ የፈጠረው ምስቅልቅል ሁኔታ!

- የአቢይ አገዛዝ በወያኔ የተሳሳተ የትረካና የጥፋት መንፈስ የታነፀ ነው።
- ማለትም የራሱ የሆነበምሁራዊ ርዕይ የታነፀ  ዕይታ የሌለው ነው።
- ስለሆነም ፖለቲካን ወደ ተንኮልና አገርን ወደ ማከረባበት የለወጠ አደገኛ ኃይል ነው።
- የአቢይ አገዛዝ ልክ እንደ ወያኔ አገዛዝ የአሜሪካና የተቀረው ኢምፔሪያሊስት ኃይሎች ፕሮጀክት ነው።
- ከፖለቲካ አንስቶ፣ እስከማህበራዊና የኢኮኖሚ ፖሊሲ ድረስ የሚያካሂደው ፖሊሲ አገርን የሚበታትንና ህዝብን የሚያዳክም ነው።
- እስካሁን ድረስም ተግባራዊ ያደረገው የኢኮኖሚ ፖሊሲ ኒዎ-ሊበራሊዝም የሚባለውን ሲሆን፣ ይህም የዓለም አቀፍ ኮሙኒቲውን ጥቅም የሚያስጠብቅ ነው።
- ይህ ፖሊሲ እንደምናየው ድህነትን የሚያስፋፋና ህዝባችንን በኑሮ ውድነት የሚያሰቃይ ነው።
- በኦርቶድክስ ሃይማኖት ቤተክርስቲያን ላይ የሚያካሂደው ዘመቻ ሌላው የኢምፔሪያልስቶች ፕሮጀክት ነው።
- የኦርቶዶክስ ሃይማኖትና የአማራ ብሄረተኝነት ሲዳከሙ ብቻ ነው አገርን ማዳካመና መበዝበዝ የሚቻለው።
- ለብዙዎቻችን ግልጽ ያልሆነው ይህ ጉዳይ ነው። ይህ ጉዳይ ግልጽ ሲሆን ብቻ ነው ዕውነተኛ ትግል ማካሄድ የሚቻለው።
- ይህን ዐይነቱን በጣም አደገኛ አገዛዝ ለማስወገድ ከተፈለገ በዕውቀት ላይ የተመሰረተ ድርጅት ያስፈልጋል።
- በተቀነባበረ ድርጅታዊ መሰረትና በጠራ ዕውቀት አማካይነት ብቻ ነው ዕውነተኛ ነፃነትን መጎናጸፍ የሚቻለው።
- ስለሆነም ከደሙ ንጹህ የሆነና ከኢሜሪያሊስቶች ጋር ያልተሳሰረ ድርጅታዊ ኃይል በጣም አስፈላጊ ነው።

# የኢትዮጵያዊነት ፈተናውና  መፍትሄው   !

- ወያኔ የቀበረው ቦንብ ፈንድቶ አገራችንን ትልቅ ፈተና ውስጥ ሊጥላት ችሏል፡፡
- የዛሬው የአገራችንና አጠቃላዩ የዓለም ሁኔታ እንደኛ ያሉ ደካማ አገሮችን የመኖር ሁኔታ የሚፈታተኑ ናቸው፡፡
- በዛሬው ዘመን በጥቂት ኃያላን መንግስታት የማን አለብኝነት አካሄድ አገሮች እየፈራረሱ ነው፡፡
- ሊበራሊዝምንና የነፃ ንግድን እናስፋፋልን በማለት አገሮች ህልውናቸው እንዲፈራርሱ የተደረገ ነው፡፡
- ያለፈው ሰላሳ ዐመታት የግሎባላይዜሽን ሂደት ብዙዎቻችንን ግራ ያጋባና ማንነታችንን የተፈታተነ ነው፡፡
- በየአገሩ በስልጣን ላይ የተቀመጡ በመሰረቱ ዘራፊ መንግስታት የየአገሮቻቸውን የመጥፋት ወይም የመበታተን ሂደት እያፋጠኑ ነው፡፡
- ከግሎባላይዜሽን ጋር ሰተት ብለው የገቡ ቆሻሻ ባህሎች የአገራችንን ብሄራዊ ነፃነትና ክብር እየተፈታተኑ ነው፡፡
- በተለይም ወጣቱ አቅጣጫውን እንዲስት እያደረጉ ነው፡፡
- በዚህ ላይ የጫአት መቃምና ሌሎች ዕፆች መስፋፋታቸው  የታዳጊውን ወጣት አስተሳሰብ አዛንፈውታል፡፡
- ነዘህላል እንዲሆን አድርገውታል፡፡ ግብረ-ሰዶማዊት መስፋፋቱ ሌላው አስከፊ ገጽታ ነው፡፡
- ይህ ዐይነቱ እንደኛ ያሉ አገሮችን መፈታተንና በተለያየ መልክ ማዳከም የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝምና የተቀረው
- የምዕራቡ ካፒታሊስት ዘለዓለማዊ ፕሮጀክት ነው፡፡
- አንድ አገር በብዙ አቅጣጫ ስትወጠር አንድ ህዝብና መንግስት መስራት የሚገባቸውን ነገር እንዳይሰሩ ይገደዳሉ፡፡

# መፍትሄው !

- በመጀመሪያ በመሀከላችን የጠራ አመለካከት መኖር አለበት።
- በሃሳብ ዙሪያ መሰባሰብ አለብን።
- ይህ አስተሳሰብ ሳይንሳዊ፣ ፍልስፍናዊና የቲዎሪ መሰረት መኖር አለበት።
- ለአገር ደህንነትና ብልጽግና እንታገላለን የሚሉ ኃይሎች በፕሪንስፕል መመራት አለባቸው።
- እያንዳንዱ ተጎታች ሳይሆን የህሊናው ተገዢ መሆን አለበት።
- ክሪቲካል አመለካከትን ማዳበር እጅግ አስፈላጊ ነው።
- ክርክርንና ውይይትን ማስቀደም አስፈላጊ ናቸው።
- ክርክር የማይደረግበት አካሄድ ሃሳብን ያቀጭጫል፤ ዕድገት እንዳይኖር ያደርጋል።
- አስተሳሰባችንን መቀየር አለብን።
- በታሪክ ውስጥ የጭንቅላት ተሃድሶ ያልተካሄደበት አገር ውጤታማ ሊሆን አይችልም።
- ለስልጣን አለሁ አለሁ የሚለው አካሄድ መቆም አለበት።
- የአገርንና የህዝብን ጥቅም ማስቀደም የሚለው መመሪያ መቅደም አለበት።
- ለመታዘዝ የሚዘጋጅ እንጂ አገራችን አዛዥ አትፈልግም።
- ከዚህ ስንነሳ የአገራችን የተወሳሰበ ችግር የብሄረሰብን መብት በማወቅ የሚፈታ አይደለም።
- የሁሉም ብሄረሰቦች ችግር በሳይንሳዊ መነጽር የግለሰብ ነፃነትን በማወቅ የሚፈታ ነው።
- እያንዳንዱ ግለሰብ የዚህ ወይም የዚያ ብሄር አባል በመሆኑና መብቱ ይጠበቃል ቢባል የሚያገኘው ጥቅም የለም።
- በታሪክ ውስጥም አልታየም።
- ስለዚህም ሬፑብሊካዊ አገዛዝ በክፍለ-አገር ደረጃ በማዋቀር ፌዴራላዊ አገዛዝ ጋር መያያዝ አለበት።
- አገርን ማስተዳደርና ማበልጸግ የሚቻለው በዕውቀትና በችሎታ አማካይነት ነው።
- ለዚህም ሰብአዊነትን ማስቀደምና ማስተማር አስፈላጊ ነው። ዶ/ር ፈቃዱ በቀለ አመሰግናለሁ !!